# የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

# ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ግንዛቤ ማስጨበጫ የስልጠና ማኑዋል

የካቲት 2007 ዓ ም

አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ

1. መግቢያ ..... 3
2. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ምንድነው? ..... 4
2.1. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ተግባራት ..... 5
3. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር መንስኤዎች ..... 5
3.1. የግንዛቤ ችግር ..... 5
3.2. የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ተደራሽነት አናሳ መሆን ..... 6
3.3. የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦት አናሳ መሆን ..... 7
3.4. የሙያ ስነ-ምግባር ጉድለት ..... 10
3.5. የንግድ ሁኔታዎች ምቹ አለመሆን ..... 10
3.6. ቅንጅታዊ አሰራር ጉድለት ..... 11
3.7. ከአጎራባች አገሮች የምንጋራቸዉ ድንበሮች ለኮንትሮባንድ ንግድ አመቺ መሆን ..... 12
3.8. ጥብቅ የቁጥጥር ስርዓት ያለመኖር ..... 13
3.9. የቴክኖሎጂ እድገት ..... 14
4. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚካሄድባቸው ቦታዎች ..... 14
4.1. በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ..... 14
4.2. በመካከለኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ..... 15
4.3. በዝቅተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ..... 17
5. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ተሳታፊ አካላት ..... 17
5.1. የማህበረሰብ እንስሳት ጤና ሠራተኞች (CAHWS) ..... 17
5.2. ከተለያዩ የእንስሳት ጤና ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸዉን ያጠናቀቁ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ..... 18
5.3. የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገ ወጥ መንገድ በዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች ..... 18
5.4. የሰው መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች ..... 18
5.5. ህጋዊ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች ..... 19
5.6. በመንግስት የእንስሳት ጤና ክሊኒክ የሚሰሩ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ..... 19
5.7. ተጠቃሚው ህብረተሰብ ..... 19
5.8. የቁጥጥር ጣቢያዎች ..... 20

6. ህገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚካሔድባቸው መንገዶች....................20
7. ህገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚያስከትላቸው ችግሮች....................21
7.1. በእንስሳት ጤናና ምርታማነት ላይ የሚያስከትለው ችግር....................21
7.2. በማህበረሰብ ጤናና በአካባቢ ደህንነት ላይ የሚያስከትለው ችግር....................22
7.3. በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ችግር....................23
8. ህገ- ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን ለመግታት መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች....................24
8.1. የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳዳግ....................24
8.2. የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦትን ማሻሻል....................25
8.4. የሙያ ስነ-ምግባር ጉድለትን ማሻሻል....................25
8.5. የንግድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት....................26
8.6. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት....................26
8.7. የቁጥጥር ተግባራትን ማጠናከር....................26
8.8. ህጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ....................27
9. በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ቁጥጥር የባለድርሻ አካላትና የተገልጋዩ ተግባርና ኃላፊነት....................29
9.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ....................29
9.2. የክልል እንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ/ግብርና ቢሮ/....................30
9.3. የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች....................30
9.4. ባለድርሻ አካላት....................31
9.5. በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች/ባለሃብቶች....................32
9.6. ተጠቃሚው ህብረተሰብ....................32
10. ማጠቃለያ....................33

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ 53.99 ሚሊዮን የቀንድ ከብቶች፣25.5 ሚሊዮን በጎች፣24.06 ሚሊዮን ፍየሎች፣9.01 ሚሊዮን የጋማ ከብቶች፣0.92 ሚሊዮን ግመሎች፣50.38 ሚሊዮን ዶሮዎች እና 5.21 ሚሊዮን የንብ ቀፎዎች ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ይሁን እንጂ የእንስሳት ሀብት ልማቱ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከ12-16 ፐርሰንት ብቻ እንደሆነ ይገለፃል፡፡ ለእንስሳት ምርትና ምርታማነት መቀነስ ዘርፈ ብዙ ምክንያቶች ቢጠቀሱም የመኖ አቅርቦት እጥረት፣ የምርታማ እንስሳት ዝርያ ማነስና የእንስሳት ጤና ችግሮች ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ በተጨማሪ በሀገሪቱ ለእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፉ የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋትም በእንስሳት ጤና ችግርና ምርታማነት መቀነስ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማቀጨጭ ሀገሪቱ ከእንስሳት ሀብት ማግኘት የሚገባትን ምርት እንዳታገኝ የሚያደርግ ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ህገ ወጥ ተግባር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በማህበረሰብ ጤና ላይ የሚያስከትለው ችግርም ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም ጥራቱ፣ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድኃኒት ለአርሶ/አርብቶ አደሮችና በእንስሳት እርባታ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች እንዲደርስ በማድረግ፣ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ችግርን ለመቅረፍ የቁጥጥር ስልት በመንደፍና በመተግበር እንዲሁም ባለድርሻ አካላትንና ተገልጋዮችን ቀጣይነት ባለውና ውጤት በሚያመጣ ሁኔታ በማሳተፍ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ ሀገሪቱ ከዘርፉ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ እንድታገኝ የቁጥጥርና የአስተዳደር ተግባራት በቅንጅት እንዲሰራ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 728/2004 በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተቋቁሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 272/2005 ፀድቆ በስራ ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች (ሞያሌ፣ጅጅጋ፣መተማ፣ትግራይ፣ሁመራ፣ባህርዳር፣ጅማ፣ሚዛን፣አዳማ፣ድሬዳዋ፣አዲስ አበባ) በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት አካሂዷል፡፡ ከዳሰሳ ጥናቱ የተገኘውንም ውጤት በተለያዩ መድረኮች ቀርቦ ከባለድርሻ አካላትና ከተገልጋዮች ጋር በመወያየት አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ከተለያዩ መድረኮች

እንደተገለጸውና የዳሰሳ ጥናት ውጤቱም እንደሚያሳየው ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በአንዳንድ ህጋዊ ባልሆኑና ሙያዊ ስነምግባርን አክብረው በማይሰሩ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ጭምር እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት ንግድን በሚመለከት ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች በማያከብሩ ህጋዊ ነጋዴዎች የሚፈጸም እኩይ ተግባር ነው።

ለህገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር መስፋፋት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች ውስጥ ዋናው ህበረተሰቡ ስለ ህገ ወጥ ንግድና ዝውውር ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑና የሚያስከትለውን ጉዳት ጠንቅቆ አለማወቅ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል።

ስለሆነም ይህንን ለሕብረተሰብና እንስሳት ጤና ብሎም ለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት እንቅፋት ሆኖ የቆየውን ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በዘላቂነት ለመቆጣጠርና እንዲጠፋ ለማድረግ በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ በቂ ግንዛቤ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይህንን የስልጠና ማኑዋል አዘጋጅቷል።

## 2. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ምንድነው?

**ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ፡-** ማለት ስለ እንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አሠራር የወጣውን አዋጅ እና በተዋረድ አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ መመሪያዎችን አሠራር ባልጠበቀ መልኩ የእንስሳት መድኃኒቶችን ማምረት፣ማስመጣትና መላክ፣እንደገና ማሸግ፣ማከማቸት፣ማጓጓዝ፣በጅምላ ማከፋፈልና በችርቻሮ ማደል ሲሆን ከእንስሳት መድኃኒት ጋር የተያያዘ ሙያ ሳይኖራቸውና የሙያ ፍቃድና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አግባብ ካለው አካል ሳያወጡ በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ሥራ ላይ መሰማራትን እና በዘርፉ በህግና ደንብ የተከለከሉ ተግባራትን ሁሉ ማከናወንን ያጠቃልላል ።

## 2.1. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ተግባራት

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ በተለያዩ ተግባራት የሚገለፅ ሲሆን በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መድኃኒቶችን ጨምሮ ያለ እንስሳት መድኃኒት ንግድ ሙያ ፈቃድና ያለምዝገባ ፈቃድ የእንስሳት መድኃኒትን ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ ማከፋፈልና ያለማዘዣ ወረቀት ማደልን የሚያካትት ነው። በተጨማሪም በህጋዊ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ሽፋን ከህገ-ወጥ መንገድ የተገኙ የእንስሳት መድኃኒቶችን መግዛትና መሸጥ፣ የእንስሳት መድኃኒትን ፈቃድ ለሌለው አካል በጅምላ መሸጥ፣የንግድ ፈቃድ ኖሯቸው ከተመዘገቡበት የንግድ አካባቢና ደረጃ ዉጪ የንግድ ሥራ ማካሄድ፣ ፈዋሽነቱ በላቦራቶሪ ያልተረጋገጠና የመጠቀሚያ ጊዜው (Expired date) ያለፈበት የእንስሳት መድኃኒት ለተጠቃሚ እንዲደርስ ማድረግ፣ ትክክለኛውን መድኃኒት አስመስሎ መስራት፣ለመድኃኒት አያያዝ ተስማሚ ባልሆነ ቦታ መድኃኒቶችን ማስቀመጥና መሸጥ፤ በአጠቃላይ በህግ የተከለከሉ ተግባራትን ማከናወን ጭምር ያጠቃልላል።

## 3. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር መንስኤዎች

በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች ለህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር መስፋፋት ብዙ ምክንያቶችን ማንሳት እንደሚቻል ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በ2006 ዓ.ም ያካሄደው የዳሰሳ ጥናት ያመላክታል። ሆኖም እንደየአካባቢው ሁኔታ ምክንያቶቹ የሚለያዩ ቢሆንም የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

### 3.1. የግንዛቤ ችግር

መድኃኒቶች ከአመራረታቸው ጀምሮ አገልግሎት ላይ እስከሚደርሱበት ጊዜ ድረስ ተገቢውን አያያዝና ጥንቃቄ ካልተደረገላቸው በስተቀር ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው እንደሚያመዝን ግልፅ ነው። ችግሩን ከባድ የሚያደርገው ደግሞ በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም በህገወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር ላይ የህብረተሰቡ፣የባለድርሻ አካላት፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችና የባለሙያዎችም ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑና በእንስሳትና በሰው ጤና ላይ ብሎም በአገር ኢኮኖሚ የሚያስከትለውን ጉዳት በተገቢው መንገድ አለመረዳቱ ይሆናል። በዚህ ረገድ አሁንም ድረስ ለሁሉም አካላት ቀጣይነት ባለው መልኩ የማስገንዘቢያ ማስጨበጫ ትምህርት እየተሰጠ ባለመሆኑ እና በቂ ግንዛቤ ባለመፈጠሩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሁሉም

በየደረጃው የህገ ወጥ መድኃኒት ንግድና ዝውውሩ ተሳታፊ ሲሆን ይታያል። ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ብዙ አርሶ/አርብቶ አደሮች በእነሱ ደረጃ ለእንስሳቶች መሰጠት የሌለባቸውን የእንስሳት መድኃኒቶች( በመርፌ የሚሰጡ መድኃኒቶችን ጭምር ) በህገ ወጥ መንገድ ከእንስሳት መድኃኒት ንግድ ተቋማት በመግዛት ለእንስሳት እየሰጡ እንደሆነ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አንድ በሰሜን ጎንደር ዞን የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ፈቃድ ባለሙያ ላልሆነ ሰው የሙያ ፍቃዳቸውን በማከራየት ችግሩ የበለጠ እንዲባባስ እያደረጉ ያሉ መሆኑ እና ስለ እንስሳት መድኃኒት አያያዝና ጠቃቀም ግንዛቤ የሌላቸው ግለሰቦችም በመድኃኒት ንግድ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ የጥናቱ ውጤት ያረጋግጣል። የእንስሳት መድኃኒትን ከፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጋር አደባልቀው በሸቀጣሸቀጥ ሱቅና በገበያ ላይ መሸጥም የተለመደ ተግባር ነው።

በተጨማሪም በእንስሳት መድኃኒት ፋርማሲዎችና መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ የእንስሳት ክሊኒኮች የተገዙ፣ የተሰራጩና ጥቅም ላይ የዋሉ መድኃኒቶችን በተመለከተ መረጃ መያዝና (record keeping) ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ የተለመደ ባለመሆኑ የቁጥጥሩን ስራ አሰቸጋሪ ያደርገዋል። በሰው መድኃኒት መሸጫ ንግድ ድርጅቶችና መድኃኒት ቤቶችም የእንስሳት መድኃኒት ተቀላቅለው እንደሚሸጡ በተለያዩ መድረኮች ተገልጿል። በአጠቃላይ በሁሉም አካላት ዘንድ የግንዛቤ ችግር መኖሩ ለህገ ወጥ ንግድና ዝውውሩ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ማወቅ ይቻላል።

### 3.2. የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ተደራሽነት አናሳ መሆን

የእንስሳት ጤናን በመጠበቅ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ተደራሽነት በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች መስፋፋት እንዳለበት ይታመናል። ኢትዮጵያ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳት ሲኖሯት ብዙዎቹ ደግሞ በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በባህላዊ የእርባታ ዘዴ ስር የሚገኙ ናቸው። በሀገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች ማለትም በደቡብ ምስራቅ (ቦረና)፣ሰሜን ምስራቅ (አፋር) በምስራቅ (ሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት)፣ በምዕራብ (ጋምቤላ)፣ በደቡብ ምዕራብ (ደቡብ ኦሞ) የሚኖሩ ህዝቦች ህይወታቸው በሙሉ የተመሰረተው በእንስሳት እርባታ ሲሆን በተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት የእንስሳት ግጦሽና ውሃ እጥረት ስለሚያጋጥማቸው በተለያዩ ወራት እንስሳትን ከቦታ ወደ ቦታ ከማዘዋወራቸው ጋር ተያይዞ ለተለያዩ የጤና ችግሮች ይጋለጣሉ። በሌላ በኩል በእነዚህ አካባቢዎች የመንግስትም ሆነ የግል እንስሳት ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትና

ባለሙያ እጥረት ይታያል፡፡ ብዙዎች የግል የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ተቋማት የሚገኙት በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍል በከተሞች አካባቢ ነው፡፡ ይህም በተጠቀሱት አካባቢዎች ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

የኢትዮጵያ እንስሳት ሀኪሞች ማህበር የእንስሳት ሀኪም ለእንሰሳት በሚል መርሀ ግብር 1:200,000 ለመከላከል፣ 1:10-30,000 የእንስሳት በሽታ አልፎ አልፎ ለሚታይባቸው ቦታዎችና 1:1-5000 ሙሉ የእንስሳት አገልግሎት ማግኘት ለሚገባቸው ቦታዎች የሚል ንጽጽር አስቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ በተጨባጭ ያለው እውነታ እንደሚያመለክተው በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት በአሁኑ ወቅት በእንስሳት ጤናው ዙሪያ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በመስራት ላይ ሲሆን በአገሪቱ በሚገኙ በተለያዩ የትምህርት ተቋማት የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን የእንስሳት ሀብቱ በብዛት በሚገኝበት በአርሶ/አርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲመደቡ በማድረግ ችግሩን ለማቃለል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም ችግሩን ለመቅረፍ መንግስት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም በጥናት ለማረጋገጥ እንደተቻለው አሁንም በአርሶ/አርብቶ አደር አካባቢዎች ተደራሽነቱ አናሳ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠቃሚዎች ህገ ወጥ መድኃኒት በመግዛት እንደሚጠቀሙና ከህገወጥነቱ ባሻገር ከባለሙያ ውጪ ስለሆነ ለፀረ ተህዋስያን መላመድ ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ በአጠቃላይ ለህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር የህክምና አገልግሎት ተደራሽነት የበኩሉን አሉታዊ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

### 3.3. የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦት አናሳ መሆን

የእንሰሳት መድኃኒት እጥረትን ለማቃለል በመንግስት መ/ቤት ከሚቀርበው መድኃኒት ባሻገር ተጠቃሚው ህብረተሰብ በየአካባቢው አገልግሎቱን በተሻለ መንገድ እንዲያገኝ ለማድረግ በዘርፉ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶችን የማበረታታት ስራ በመንግስት በኩል እየተሰራ ያለ ስራ ነው፡፡ ነገር ግን አሁንም የእንስሳቱ ቁጥርና የበሽታው ስርጭት ጎልቶ በሚታይበት በአርሶ/አርብቶ አደሩ አካባቢዎች እጥረቱ በጥራትም ይሁን በመጠን እንዳለ የሚታይ ጉዳይ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶችም በአሁኑ ጊዜ በስፋት በመሀል ሀገር ብቻ ተወስነው የሚሰሩ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ በአንዳንድ ክልሎችና ወረዳዎች ለእንስሳት መድኃኒት ግዥ የሚመደበው በጀት የእንስሳት

ቁጥርንና የበሽታውን ስርጭት ያላገናዘበ አነስተኛ በጀት ሲሆን በመንግስት መ/ቤት የሚቀርበው መድኃኒትም ከ20-30% እንደማይበልጥ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ተጠቃሚው ህብረተሰብና ባለሙያዎችም ጭምር ክፍተቱን ለመሸፈን ጥራቱና ፈዋሽነቱ ያልተረጋገጠና በህጋዊ መንገድ ያልተገኘ መድኃኒት እንደሚጠቀሙ ግልጽ ነው፡፡ ይህም እንደሚያሳየው የመድኃኒት አቅርቦት ችግር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ነው፡፡

በአጠቃላይ የእንስሳት መድኃኒት ከዉጪ ወደ ሀገር ዉስጥ ሲገባ በአገሪቱ የሚታዩ የእንስሳት በሽታዎችን አይነትና ስርጭትን ግምት ዉስጥ ያስገባ ስላልሆነ የሚቀርበዉ የእንስሳት መድኃኒት የተጠቃሚዉን ፍላጎት የሚያረካ አይደለም፡፡ ብዙዎች የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስገቧቸው መድኃኒቶች ተመሳሳይ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ተህዋስያንን የተላመዱ ናቸው፡፡ ብዙ መድኃኒቶችን እንደ ማደንዘዣ (anesthesia)፣ የህመም ማስታገሻ መድኃኒቶች (anti inflammatory drugs)፣ ሚኒራልና ቫይታሚን (calsium boroguloconet and vitamines) እና የመሳሰሉት ገበያ ላይ ለማግኘት እንደሚቸገሩ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ የእንስሳት መድኃኒት ተጠቃሚ አካላት የተገኘውን መንገድ እንዳማራጭ በመጠቀም በማንኛውም ቦታና ግለሰብ የተገኘን መድኃኒት ለመግዛት ይገደዳሉ፡፡ ህገ-ወጥ ነጋዴዎችም ይህንን ችግር እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅመው ጊዜው ያለፈበትንና ማንኛውንም ለእንስሳት በሽታ ፈዋሽነቱ ያልተረጋገጠ መድኃኒት ለተጠቃሚው ይሸጣሉ፡፡

## የተመዘገቡ የእንስሳት መድኃኒቶችና የአስመጪዎችነን ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የመድኃኒቶች ስም | የአሰመጪዎች ብዛት |
|---|---|
| Ivermectin 1% injection | 11 |
| Tetramisole HCL +oxyclozanide | 12 |
| Oxytetracycline | 22 |
| Penestrep 20 % injectaion | 4 |
| Multi vitamin injection | 2 |
| **Lactaclox 5G** (Cloxacillin 200mg, Ampicillin 75mg) | 1 |
| Albendazole | 8 |
| FENBENDAZOLE | 7 |
| TETRAMISOLE | 2 |
| Isometamidium chloride | 13 |
| SULPHAMETHOXAZOLE-TRIMETHOPRIM | 1 |
| Diminazine | 13 |
| AMPROLIUM 20 PERCENT POWDER | 2 |
| Triclabendazole | 5 |
| Tetramisole HCL | 4 |
| oxyclozanide | 3 |
| Fenoflox 10%(Enrofloxacin) injection 100ml injectable | 1 |
| Medicated pet shampoo concentrate 1*20 liter drum | 1 |
| Deltametrin 1% pour w/v (smash 1% pour-on) | 1 |
| Diazinol 60% | 1 |
| Amitraz | 1 |
| Sthetoscope specially designed for vet use standard model | 1 |
| Termometer | 1 |
| Chromic catgut cassette USP3/0,100meter | 1 |

## 3.4. የሙያ ስነ ምግባር ጉድለት

እንደሚታወቀው የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት ለህብረተሰቡ አጠቃላይ ስለ እንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም፣ ስለ ህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት በህጋዊ መንገድ የተገኙ መድኃኒቶችን በመያዝ፣ በማዘዝ፣ በማደልና ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ የእንስሳትን ብሎም የህብረተሰቡን ጤንነት በመጠበቅ ለምርትና ምርታማነት መሻሻል የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ነው። ሆኖም አንዳንድ የሙያ ስነምግባሩን የማያከብሩና የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚያስተውሉ ባለሙያዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ህገ ወጥ የመድኃንት ንግድና ዝውውርን ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆችን፣ደንቦችንና የአሠራር መመሪያዎችን ባለማክበር የሙያ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖራቸው መድኃኒቶችን በህገ ወጥ መንገድ በመግዛት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ማደል ወይም መሸጥ፣ በመንግስት መ/ቤት በኩል በጨረታ መድኃኒት በሚገዙበትም ወቅት ህገወጥ ተግባራትን መቆጣጠር ሲገባቸው ከህገ ወጥ አስመጪዎች ጋር በጥቅም በመተሳሰር ያለህጋዊ ሰነድ እንዲጫረቱ በማድረግ እና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ መድኃኒት በሚያድሉበት ወይም በሚሸጡበት ወቅት ህጋዊ ማዘዣ ወረቀት /ደረሰኝ አለመጠቀማቸው ብሎም በህገወጥ ንግድና ዝውውሩ መሳተፋቸው ቁጥጥሩን ከባድ ያደርገዋል። በመሆኑም የባለሙያዎች የሙያ ስነምግባር ችግር ለህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር መስፋፋት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል።

## 3.5. የንግድ ሁኔታዎች ምቹ አለመሆን

በእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በኩል የሚታየውን ክፍተት መስመር ለማስያዝ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በመንግስት በኩል ተቋቁሞ የአስተዳደርና የቁጥጥር ስራዎችን በመስራት ችግሩን ለማቃለል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ማንኛውም ግለሰብ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው በንግድ ፍቃዱ ብቻ እንደማንኛውም ሸቀጣ ሸቀጥ በማንኛውም ቦታ ይዞ በመገኘት ለተጠቃሚዎች ሲያቀርብና ሲሸጥ እንደነበር ግልፅ ነው። አሁንም ቢሆን የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የአሰራር መመሪያዎችን በማዘጋጀት በስራ ላይ እንዲውሉ ያደረገ ቢሆንም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በሁሉም አካባቢዎች ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ምቹ የሆነ የንግድ ሁኔታዎች በመፍጠር ረገድ ክፍተቶች እንዳሉ ይስተዋላል። ከዚህ በተጨማሪም

በቁጥጥርና ፍተሻ ጣቢያዎች የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮች፣ ወደብ ላይ ለንግድ ምርቶች የሚከፈል ክፍያ መጠን የነጋዴዎችን የገቢ መጠን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆን፣ ምርቶች ወደብ ላይ ለረዥም ጊዜ በመቆየት የክፍያ መጠኑን ከፍ ማድረግና ነጋዴዎችን ማጉላላት ለህገ ወጥ ንግዱ እንደ ምክንያት የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ በቦታው የተደራጀ የቁጥጥርና የፍተሻ ስልት ያለመኖር፣ ዘመናዊ የአሰራር ዘዴን ያለመጠቀምና የህገ ወጥ ተግባሩን አሉታዊ ተፅፅኖ በመረዳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ተባብሮ ያለመስራት የቁጥጥር ተግባሩን ከባድ ያደርገዋል፡፡ ይህ ችግር በብዙ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ኢትዮጵያን ጨምሮ የሚታይ ነው፡፡ በ2012 እ.አ የአፍሪካ ሀገራት ወደብ አቋራጭ ንግድ ችግሮችና መፍትሄዎች በሚል ርዕስ በቀረበ ጽሁፍ ላይ እደተገለጸው በብዙ የአፍሪካ ሀገራት የንግድ ምርቶች ከሀገር ለመውጣት እና ወደገር ውስጥ ለመግባት በአማካይ 20-30 ቀናት የሚወስድ ሲሆን በሌሎች ያደጉ ሀገሮች (አውሮፓና ኤሲያ) ግን ከ 4-8 ቀናትን ብቻ ነው፡፡

### 3.6. ቅንጅታዊ አሰራር ጉድለት

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ቁጥጥር ሥራ እስካሁን ድረስ በአገራችን ትኩረት ተነፍጎት የቆየ የሥራ ዘርፍ መሆኑን በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ በተለያዩ መድረኮች ከባለሙያዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ውይይቶች ለመረዳት እንደተቻለው በዘርፉ ምንም ሥራ እንዳልተሰራና በአንዳንድ አካባቢ ባለሙያዎች ህገ ወጥ ንግድና ዝውውሩን ለመቆጣጠር የሞከሩበት አግባብ ቢኖርም ዘርፉን በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር አካል ባለመኖሩ፣ በየደረጃው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ ባለመኖሩ፣የቁጥጥር ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን የሚረዳ የአሰራር መመሪያና ጠንካራ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ሥራው ወጥነት ባለው መልኩ እየተሰራ እንዳልሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ግን ህገ ወጥ የሰው መድኃኒት ንግድና ዝውውርን ለመቆጣጠር ከላይ እስከታች በየደረጃው የተቋቋመ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ መኖሩና ኮሚቴውም ስራውን በአገባቡ ለመስራት እየተንቀሳቀሰ ያለ መሆኑን፣የገበያ ትስስሩም ቀጥታ ከላይ ወደታች በተዋረድ በመሆኑ እንዲሁም ለህብረተሰቡ በህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር ዙሪያ ያላሰለሰ የማስገንዘቢያ ትምህርት በመሰጠቱ በአሁኑ ወቅት ህገ ወጥ ንግዱና ዝውውሩ በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰበትና አመርቂ ውጤት የተገኘበት መሆኑን በተለያዩ መድረኮች ከተሳተፉ ባለድርሻ አካላትና ባለሙያዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዳሰሳ ጥናት ውጤቱ ለመረዳት እንደተቻለው መድኃኒት ወደአገር ውስጥ ከሚገባበት ጊዜ ጀምሮ ለተጠቃሚው እስከሚደርስበት

ጊዜ ድረስ አስፈላጊው ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት፣በየደረጃው ተግባሩን በአግባቡ የሚያከናውን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተቋቋመ ግብረ ሀይል ኮሚቴ መኖር እንዳለበት፣ ወጥ የሆነ የገበያ ትስስር መኖር እንደሚገባው፣ህገ ወጦችን ለመቆጣጠር የሚረዳ የአሰራር መመሪያና ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልግ እና በተጨማሪም ስለ ህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር ብሎም የሚያስከትለውን ጉዳት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ፣ ለባለሙያዎችና በዘርፉ ለተሰማሩ የንግድ ድርጅቶች የማስገንዘቢያ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት እንደሚገባ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 3.7. ከአጎራባች አገሮች የምንጋራቸዉ ድንበሮች ለኮንትሮባንድ ንግድ አመቺ መሆን

በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች ከጎረቤት ሀገሮች፤ የኢትዮጲያ ሱማሌ ( ከሱማሌ፣ሱማሌላንድ እና የኬኒያ)፤ ኦሮሚያ ክልል ከኬንያ፤መተማና ሁመራ ከሱዳንና ከኤርትራ ድንበር ጋር የሚጋሯቸው ደንበሮች ሰፊ ከመሆናቸው በተጨማሪ ጠንካራ የሚባል ቁጥጥር የሚደረግበት አይደለም፡፡ ስለሆነም የጠረፍ ወረዳዎች ከአገራችን መዲና አዲስ አበባ በርቀት የሚገኙ እንደመሆናቸው የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦትን ከመሀል አገር ለማምጣት ከትራንስፖት ወጪና እርቀት አኳያ በቅርብ ርቀት የጎረቤት አገር የድንበር ተሻጋሪ (cross border) ተፈጥሮአዊ የሆነ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትና የንግድ ልውውጥ ማድረጉ የተሻለና ተመራጭ አድርገው ስለሚወስዱ ይህ ሁኔታ ሕገወጥ ንግድን ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በዚህ መንገድ የሚገባ መድኃኒትም ወደ ዋናዉ የአገሪቱ ህገወጥ የመድኃኒት ዝዉዉር ሰንሰለት ዉስጥ ይገባል፡፡

የሞያሌ ወረዳ በሁለት ክልሎች (በኦሮሚያና ሶማሌ ክልላዊ መንግስት) የሚተዳደር ስለሆነና ቅንጅታዊ አሰራር ስላልጎለበተ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ቁጥጥር ለማድረግ አስቸጋሪ መሆን፤ የእንስሳት ጤና መሰረተ ልማት እንደ ክሊኒኮችና ጤና ኬላዎች በመድኃኒትና በውስጥ ቁሳቁሶች ተሟልተው አለመገኘትና እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢ በቅርብ አለመገኘቱ ለሕገወጥ ንግድ መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡




ስዕል1. ዋና ዋና የቁጥጥር ቦታዎች

### 3.8. ጥብቅ የቁጥጥር ስርዓት ያለመኖር

በሀገሪቱ እስካሁን ድረስ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን በተመለከተ በሁሉም አካባቢዎች ሊተገበር የሚችል የአሰራር መመሪያ ባለመኖሩና ህገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን የሚቆጣጠር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተዋቀረና በየደረጃው የተቋቋመ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ ባለመኖሩ የእንስሳት መድኃኒትን በተገቢው መንገድና በተፈቀደላቸው ድርጅቶች ወይም አካላት እንዲሰራጩ ለማድረግ ከፍተኛ ችግር ሲፈጥር ይታያል፡፡

በኢትዮጵያ ወደቦች ቦሌ አለምአቀፍ አየር መንገድን ጨምሮ የቁጥጥር ስርዓቱ የጠነከረ ባለመሆኑ የተለያዩ ሀገራት (የኢስያ፣ መካከለኛው ምስረቅና ምዕራብ አፍሪካ ሀገራት እና

አውሮፓ) ህገወጥ የመድኃኒት ነጋዴዎች እንደዋና መተላለፊያ መንገድ (transit) ይጠቀሙባታል፡፡ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ የምዕራብ አፍሪካ ሀገራት (ናይጀሪያና ሱዳን) ህገ ወጥ የመድኃኒት (አደንዛዥ እጽ) ነጋዴዎች በቦሌ አየር መንገድ ተይዘው ለህግ የቀረቡበት ሁኔታ እንዳለ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ አይነቱ ድርጊት ለሀገሪቱ ህገ ወጥ ንግድ መስፋፋት መንገድ ከፋች ከመሆን አልፎ የሀገርን መልካም ገጽታ ያበላሻል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ መድኃኒቶች ከውጪ ሀገር ከሚገቡበት ጀምሮና በአገር ውስጥም ተመርተው እስከ ተጠቃሚው እስከሚደርሱበት ጊዜ ድረስ ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ለህገ ወጥ ንግዱ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩ ባሻገር በህጋዊ መንገድ በዘርፉ የሚሰሩ ባለሀብቶችን የስራ ተነሳሽነት የሚያሳጣ ብሎም የአገርን ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

### 3.9. የቴክኖሎጂ እድገት

ቴክኖሎጂ ምንም እንኳ የአንድ ሀገር ስልጣኔ መገለጫና ለሀገር እድገት አስፈላጊ ቢሆንም አንዳንድ ግለሰቦች ቴክኖሎጂውን ባልተፈለገ መንገድ ይጠቀሙታል፡፡ የኢንተርኔት፣ ስልክና ሌሎች የተለያዩ የመገናኛ ሚዲያዎችና የመንገዶች ግንባታ መስፋፋት ለህገ ወጥ ነጋዴዎች መረጃ በቀላሉ ለመለዋወጥና ምርቶችን ከሀገር ወደ ሀገር ወይም ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም የህገ ወጥ መድኃኒት ንግድና ዝውውር የቁጥጥር ተግባሩን አስቸጋሪና ውስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 4. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚካሄድባቸው ቦታዎች

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች የሚታይ ሲሆን መገለጫዎቹም በዚያው ልክ የሚለያዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከችግሮቹ ስፋትና ክብደት አንፃር ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግደድና ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች፣ በመካከለኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎችና በዝቅተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ብሎ በመከፋፈል ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ይህም እንደችግሩ ስፋትና ክብደት የመፍትሄ አቅጣጫ ለይቶ ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡ ስለዚህ፡-

### 4.1. በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች

ህገ ወጥ ( ኮንትሮባንድ) የእንስሳት መድኃኒት ከአጎራባች አገሮች( ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ኬኒያና ሶማሊያ) ወደ ኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች እንደሚገባ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም

የተነሳ በአገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ እየተካሄደ መሆኑ ይስተዋላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋና ዋና የቁጥጥር ጣቢያዎች( መተማ፣ ጋምቤላ፣ ሐረር፣ ሶማሌ፣ ሞያሌ፣ ቦሌ) ፣ አገሪቱ ከአጎራባች አገሮች ከምትዋሰንባቸው ቦታዎች በቅርብ ርቀት የሚገኙና በከፍተኛ ደረጃ ንግድ የሚካሄድባቸው ከተሞች አድስ አበባን ጨምሮ ጅግጅጋ፣ ሐረር፣ድሬዳዋ፣ ናዝሬት፣ ድላ፣ ኮምቦልቻና ገዳማይቱ እንዲሁም በአርብቶ አደር አካባቢዎች ህገ ወጥ ወይም ኮንትሮባንድ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ  የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ናቸው ብሎ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተጠቀሱት አካባቢዎች ህገ ወጥ ንግዱና ዝውውሩ እንዲባባስ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ፡-

- ህገ ወጦች ታክስና ግብር ስለማይከፍሉ ከህገ ወጥ ንግዱ የሚያገኙትን ጥቅም ለማስከበር መድኃኒቱ በቁጥጥር ጣቢያዎች(check points) እየተፈተሸ ሳይሆን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር አቋርጦ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ስለሚደረግ
- ህገ ወጥ መድኃኒት በቅናሽ ዋጋ ስለሚሸጥና የእንስሳት መድኃኒት ተጠቃሚዎች ህገ ወጥ መድኃኒትን ለመጠቀም ፍላጎት ማሳየታቸው
- በተጠቀሱ ከተሞች ህገ ወጦች መድኃኒቶችን ለማከማቸትና ወደ ሌላ የአገሪቱ ከተሞች ለማሰራጨት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ
- በአርብቶ አደር አካባቢዎች የእንስሳት ህክምና ተደራሽነትና የመድኃኒት አቅርቦት አናሳ መሆኑ እንዲሁም የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች ያለመስፋፋታቸው
- በአንዳንድ አካባቢዎች በስራ አጥነት ሰበብ በህገ ወጥ/ኮንትሮባንድ/ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ  ስራ ላይ እየተሳተፉ ያሉ ግለሰቦች መኖራቸው
- ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ያልጎለበተ መሆኑ
- በቁጥጥር ጣቢያዎች የሚሰሩ አንዳንድ ተቆጣጣሪዎች በጥቅማ ጥቅም በመደለል ለህገ ወጦች እገዛ ስለሚያደርጉ
- በአንዳንድ አጎራባች አገራት ( ሶማሊያ ) የፖለቲካና የማህበራዊ አለመረጋጋት እንዲሁም የኢኮኖሚ ድቀት መኖሩ በኢትዮጵያ ህገ ወጥ( ኮንትሮባንድ ) ንግድ እንዲስፋፋ ስለሚያደርግ
- ህገ ወጦችን ከድርጊታቸው እንዲወጡ የሚያደርግ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ

## 4.2. በመካከለኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች

በከፍተኛ ደረጃ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኙ የክልል፣ የዞንና የወረዳ ከተሞች( ሀዋሳ፣ሻሸመኔ፣ አርባ ምንጭ፣ ሰመራ፣ጅማ፣አሶሳ፣በህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣መቀሌ፣ ጋምቤላና በመሳሰሉት ቦታዎች)፣ ለእንስሳት በሽታ መከሰት ምቹ ሁኔታን በሚፈጥሩ ቆላማና ወይና ደጋ ጥምር ግብርና በሚያካሂዱ የአገራችን አካባቢዎች ለህገ ወጦች ምቹ የገበያ ሁኔታ ስለሚኖር በመካከለኛ ደረጃ ህገ ወጥ ንግድና ዝውውር የሚካሄድባቸው አካባቢዎች ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም :-

- በተጠቀሱት ከተሞች የንግድ ሁኔታው ከፍተኛ በመሆኑ ህገ ወጥ ንግድና ዝውውሩን ለማካሄድ ለህገ ወጦች ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር
- በእነዚህ ቦታዎች የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች በህጋዊ ንግድ ሽፋን ህገ ወጥ መድኃኒት እየነገዱ መሆኑ
- ህገ ወጥ መድኃኒት በዋጋ ደርጃ ዝቅተኛ ስለሚሆን ህብረተሰቡ ህገ ወጥ መድኃኒቱን ለመጠቀም ፍላጎት መኖሩ
- ህገ ወጥ ንግድና ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚደረገው ቅንጅታዊ አሰራር ዝቅተኛ በመሆኑ
- በአንዳንድ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የእንስሳት ህክምና ተደራሽነትና የመድኃኒት አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑ
- በአርሶ/ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የጋራ ግጦሽ ቦታና ውኃ ስለሚጠቀሙ ለበሽታ መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በዚህም የተነሳ እንስሳቶቻቸው በበሽታ ስለሚጠቁባቸው ያገኙትን መድኃኒት እንዲጠቀሙ ስለሚያደርጋቸው
- በቁጥጥር ጣቢያ የሚሰሩ አንዳንድ ተቆጣጣሪዎች ህገ ወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠር በቁርጠኝነት እየሰሩ አለመሆኑ
- ህገ ወጦችን ከድርጊታቸው እንዲወጡ የሚያደርግ ጠንካራ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ

### 4.3. በዝቅተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች

በአገራችን ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በዝቅተኛ ደረጃ የሚካሄድባቸው ቦታዎች በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ደጋማ አካባቢዎች፣ በመሐል አገር የሚገኙና ንግድ በብዛት የማይካሄድባቸው ከተሞችን ያጠቃልላል፡፡ ለዚህም ብዙ ምክንያቶችን ማንሳት የሚቻል ሲሆን፡-

- በአብዛኛው የአገራችን ደጋማ አካባቢዎች አርሶ አደሮች እንስሳቶቻቸውን ግጦሽና ውሀ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ስለማያዘዋውሩ፣ የጋራ የግጦሽ ቦታ ስለማይጠቀሙና ከአግሮ ኢኮሎጂውም አኳያ ለበሽታ መከሰትና መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ስለማይፈጥር መድኃኒት በብዛት እንዲጠቀሙ አያደርጋቸውም፡፡ ከዚህም የተነሳ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በነዚህ አካባቢዎች የመካሄድ እድሉ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
- የእንስሳት ህክምና ተደራሽነትና የመድኃኒት አቅርቦት ከአርብቶ አደር አካባቢዎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ በመሆኑ እና የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች በእነዚህ አካባቢዎች እየተበራከቱ መምጣታቸው ህገ ወጥ ንግዱና ዝውውሩ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## 5. ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ተሳታፊ አካላት

በተለያዩ የውይይት መድረኮች ለመረዳት እንደተቻለውና በጥናትም ለማረጋገጥ እንደተሞከረው በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ነው፡፡ ሆኖም በዋናነት ከሚሳተፉ አካላት የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### 5.1. የማህበረሰብ እንስሳት ጤና ሠራተኞች (CAHWS)

በእንስሳት ጤና ሽፋን በኩል የሚታየውን የህክምና ባለሙያዎች ክፍተት ለመሸፈን መንግስት ለአጭር ጊዜ ማህበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ጤና ሠራተኞችን በማሰልጠን በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ይሁንና በአሁኑ ወቅት በበቂ ሁኔታ የሰለጠኑ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት እየተመረቁ በመውጣታቸውና ወደ ሥራ በመግባታቸው በአንዳንድ ክልሎች ማህበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ጤና ሠራተኞች ከዚህ ሥራ እንዲወጡ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ሆኖም ግን

አሁንም በአንዳንድ በተለይም በአርብቶ አደር አካባቢዎች(በቦረና፣ ሶማሌ፣ ደቡብ ኦሞና ጋምቤላ) የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነት የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ ማህበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ጤና ሠራተኞች በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በአንዳንድ አካባቢዎች ማህበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ጤና ሠራተኞች ከተፈቀደላቸው የስራ ድርሻና የሙያ ደረጃ በላይ በህገ ወጥ መንገድ የእንስሳት መድኃኒቶችን ለእንስሳቶች እየሰጡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 5.2. ከተለያዩ የእንስሳት ጤና ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸዉን ያጠናቀቁ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች

በእንስሳት ጤና ባለሙያ እጥረት በኩል የሚታየውን ክፍተት ለመሸፈን በተለያዩ የትምህርት ተቋማት በዘርፉ የሰለጠኑ ተማሪዎች እየተመረቁ ወደ ስራ እንዲገቡ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ሆኖም አብዛኛው ተመራቂ ተማሪ መስራት የሚፈልገው በከተሞች አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ስራ አጥነት እንዲባባስ ከማድረጉ ባሻገር የህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውሩ ተሳታፊ ሲሆኑ ይታያል፡፡

## 5.3. የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገ ወጥ መንገድ በዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች

በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ዘርፍ ማንኛውም ግለሰብ መሰማራት እንደሚችል የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም የተዘጋጁ መመሪያዎች ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም በዘርፉ ለመሰማራት አግባብ ካለው አካል ፍቃድ ማግኘትና በአዋጁና በመመሪያዎች የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት የግድ ይላል፡፡ ነገር ግን በተጨባጭ ማረጋገጥ እንደሚቻለው ፍቃድ የሌላቸው በኮንትሮባንድ ንግድ የተሰማሩ ህገ ወጥ ነጋዴዎች በብዛት የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ያልሆኑ ሲሆኑ የእንስሳት መድኃኒቶችን ከሌሎች የንግድ እቃዎች ጋር በማቀላቀል ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባትና ገበያ ላይ ከሌሎች የፍጆታ እቃዎች (ሸቀጣሸቀጦች) ጋር ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለተጠቃሚዎች እንደሚያቀረቡና እንደሚሸጡ ነው፡፡

## 5.4. የሰው መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች

በተለያዩ አካባቢዎች ከባለድርሻ አካላትና ከተገልጋዮች ጋር በተደረጉ የውይይት መድረኮች መረዳት እንደተቻለውና በተደረገውም የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት የሰው ጤና ባለሙያዎች

በንግድ ድርጅታቸው ውስጥ የእንስሳት መድኃኒት በመያዝ ለተጠቃሚዎች እየሰጡ መሆኑን ነው፡፡

## 5.5. ህጋዊ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች

የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ፈቃድ ኖሯቸው ነገር ግን በህጋዊ መንገድ ካስመዘገቧቸው መድኃኒቶች ውጪ በህገ ወጥ መንገድ ከሌሎች ድርጅቶች መድኃኒቶችን ወደ ድርጅታቸው በማስገባት ለተጠቃሚዎች እንደሚያቀርቡና በተመሳሳይ መድኃኒቶችን ወደሌላ ድርጅት በማስተላለፍ የህገ ወጥ ንግዱ ተሳታፊ እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ የችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች መድኃኒቶችን በችርቻሮ ብቻ ለተጠቃሚው መሸጥ ሲገባቸው በጅምላ እንደሚያከፋፍሉ እና ጅምላ አከፋፋዮችም በችርቻሮ እንደሚሸጡ ግልፅ ነው፡፡ በተጨማሪም በማዘዣ ወረቀት የሚሰጡ መድኃኒቶችን ያለማዘዣ ወረቀት ማደልም የተለመደ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ህጋዊ የእንስሳት መድኃኒት ነጋዴዎች የህገ ወጥ ንግዱና ዝውውሩ ተሳታፊ ሲሆኑ ይታያል፡፡

## 5.6. በመንግስት የእንስሳት ጤና ክሊኒክ የሚሰሩ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች

አንዳንድ በመንግስት የእንስሳት ጤና ክሊኒክ የሚሰሩ ስነ ምግባር የጎደላቸው ባለመያዎች መድኃኒትን ያለ ማዘዣ ወረቀት በማደል፣ በህገ ወጥ መንገድ የተገኘን የግላቸውን መድኃኒት በመንግስት ክሊኒክ በማደል፣ በመንግስት በኩል መድኃኒት በጨረታ በሚገዛበትም ጊዜ ከህገወጦች እንዲገዛ በማድረግና በአጠቃላይ ህገ ወጥ ንግድና ዝውውሩን ለመቆጣጠር ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ሲገባቸው የህገወጥ ተግባሩ ተባባሪዎች መሆናቸው ቁጥጥሩን ከባድ ያደርገዋል፡፡

## 5.7. ተጠቃሚው ህብረተሰብ

በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ሁሉም ህብረተሰብ ይብዛም ይነስም የበኩሉ ድርሻ አለው፡፡ በተለይም አርሶ/አርብቶ አደሩ በአካባቢው የእንስሳት ህክምና ተደራሽነት ሽፋን አናሳ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ  በህገ ወጥ መንገድ የሚገኝ መድኃኒት እንዲጠቀም አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛው አረሶ/አርብቶ አደር ስለ እንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ ስለሌለው በማንኛውም ሁኔታ የሚገኝ መድኃኒት እኩል የመፈወስ አቅም እንዳለው ይገነዘባል፡፡ ይህ ደግሞ የመድኃኒቱ የጎንዮሽ ችግር እንዲባባስ

ከማድረጉ ባሻገር የህገ ወጥ ንግድና ዝውውሩ እንዲስፋፋ ከፍተኛውን ድርሻ የሚያበረክት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

## 5.8. የቁጥጥር ጣቢያዎች

በአገሪቱ ውስጥ በሁሉም አካባቢዎች በየደረጃው የሚገኙ የቁጥጥር ጣቢያዎች ማንኛውም ወደአገር የሚገባም ይሁን በአገር ውስጥ የሚዘዋወር የእንስሳት መድኃኒት በጣቢያዎች በሚያልፍበት ጊዜ እየተፈተሸ ህግና ደንቡ በሚያዘው መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ መልካም የገበያ ትስስር በአገሪቱ ውስጥ እንዲመቻች ማድረግ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ዘርፍ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ ስላልተፈጠረና ቅንጅታዊ አሰራሩ በአግባቡ እየተሰራ ስላልሆነ የህገወጥ ንግድና ዝውውሩ ቁጥጥር የላላ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ የቁጥጥር ጣቢያዎች የሚሰሩ ተቆጣጣሪዎች በጥቅም በመደለል መድኃኒቱን በመደበቅና በማሳለፍ እንደሚተባበሩም ይገለፃል፡፡

## 6. ህገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚካሔድባቸው መንገዶች

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ነጋዴዎች የእንስሳት መድኃኒቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ከቦታ ቦታ ለማዘዋወርና ለመሸጥ የተለያዩና ውስብስብ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡

- የማይፈተሹ ተሽከረካሪዎችን መጠቀም

  በሀገራችን በብዙ ቦታዎች  የመንግስት መስሪያ ቤትና የጉብኝት ተሽከርካሪዎችን መፍተሽ የተለመደ አይደለም፡፡ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የኮንትሮባንድ ንግድ ይካሄዳል፡፡

- ለፍተሻ የማይመቹ ሁኔታዎች መፍጠርና ሙስና

  ይህ በብዛት በመውጫና መግቢያ በሮች የሚፈጸም የማጭበርበር ስልት ነው፡፡ የፍተሻ ኬላዎችን በሌላ ተለዋጭ መንገድ በመጠቀም፣ የማይፈተሹ መጓጓዣዎችን ( ሞተር ሳይክል፣ ጋሪ፣ እንስሳትንና መንገደኛ ሰዎችን) በመጠቀም ያሳልፋሉ፡፡ ተቆጣጣሪ አካላትን በጥቅም መደለልም በስፋት የተለመደ ተግባር ነው፡፡

- ፖስታ

በተለይ በሀገርና አለምአቀፍ ደረጃ የተከለከሉና ለዝውውር ቀላል የሆኑ መድኃኒቶችን (ሀሸሽ፣ ናጫት የመሳሰሉትን) ለማዘዋወር የሚጠቀሙበት መንገድ ነው፡፡

- የቁጥጥር ስርዓቱ የተጠናከረ ስላልሆነ በሕጋዊ መንገድ እንዲገቡ ከተፈቀዱ ምርቶች ጋር ደባልቆና በተለያዩ አልባሳት መደበቅ የተለመዱ ተግባራት ናቸው፡፡
- ከቁጥጥር ጣቢያዎች ውጪ በሆኑ ቦታዎች
  በአብዛኛው በኮንትሮባንድ ወደአገር ውስጥ ገበያ የሚቀላቀሉትና በአገር ውስጥም ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩት ከቁጥጥር ጣቢያዎች ዉጪ በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

## 7. ህገ-ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚያስከትላቸው ችግሮች

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ችግሮች በተለያየ መንገድ የሚገለፅ ሲሆን በእንስሳት እና በማህበረሰብ ጤና ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት ባሻገር የሀገርን ገጽታና ኢኮኖሚ በእጅጉ ይጎዳል፡፡

### 7.1. በእንስሳት ጤናና ምርታማነት ላይ የሚያስከትለው ችግር

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በተለያዩ አካባቢዎች ግለሰቦች በህገ ወጥ መንገድ የእንስሳት መድኃኒትን እንደማንኛውም ዕቃ በየሱቁና በየገበያው እንደሚሸጡ፣ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ተቋማት ያለ ባለሙያ ማዘዣ ወረቀት መድኃኒቶችን ለግለሰቦች እንደሚሸጡ፣ በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ተቋማት ውስጥ መድኃኒት እየሸጡ ያሉ ከሙያው ውጪ የሆኑ ግለሰቦች መሆናቸውን እና በኮንትሮባንድ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ መድኃኒቶች እየተበራከቱ ያለ መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም ህገ ወጥ የግብይት ስርዓቶች መስፋፋታቸው ለፀረ-ተህዋስያን መላመድ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር መረዳት የሚያዳግት አይሆንም፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች በተለይም በአርብቶ አደር አካባቢዎች ከተጠቃሚዎች ለመረዳት እንደተቻለው አብዛኛውን መድኃኒት ሙያተኛ ካልሆኑ ህገ ወጥ የእንስሳት መኃኒት አዘዋዋሪዎች በመግዛት እራሳቸው ለእንስሳቶቻቸው እንደሚሰጡና እንስሳቶቹም ከበሽታው የመፈወስ እድላቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መድኃኒቶች ከአመራረታቸው ጀምሮ ለተጠቃሚው እስከሚሰጡበት ጊዜ ድረስ በሚመለከተው ባለሙያ አስፈላጊው አያያዝና ጥንቃቄ ካልተደረገባቸው እንዲሁም ጥቅም ላይ እንዲውሉ

ካልተደረጉ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ከማመዘኑም ባሻገር አግባባዊ ያልሆነ የመድኃኒት አጠቃቀም እንዲስፋፋና ተህዋስያን መድኃኒቶችን እንዲላመዱ ያደርጋል። በዚህም የተነሳ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በእንስሳት ጤናና ምርታማነት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ነው።

## 7.2. በማህበረሰብ ጤናና በአካባቢ ደህንነት ላይ የሚያስከትለው ችግር

በሀገራችን ብዘዎች ከ 60% በላይ የሚሆኑ በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰውና ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ (zoonotic) ናቸው። በመሆኑም ጤነኛ ያልሆነና ጥራት የሌለው የእንስሳት ተዋፅኦ የተመጋቢውን ህብረተሰብ ጤና ያውካል። አንዳንድ የእንስሳት መድኃኒቶች ለሰዎች ህክምና የተከለከሉ ናቸው። እንስሳት እነዚህን መድኃኒቶች ከወሰዱ በኋላ መድኃኒቱ ከሰውነታቸው ሳይወገድ ምርቶቻቸው ለምግብነት ይውልና ሰዎችን እስከሞት የሚያደርስ አደጋ ይገጥማቸዋል። በሌላ በኩል ለእንስሳትና ለሰው ህክምና የሚውሉ ብዙ መድኃኒቶች አሉ። የነዚህ መድኃኒቶች ቅሪት የያዘ የእንስሳት ተዋጽኦ ለምግብነት ከዋለ ሰዎች ላይ በተመሳሳይ መልኩ የመድኃኒት መላመድን ያስከትላል። ችግሩን ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በየአካባቢው መስፋፋቱ ሲሆን ይህም በመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም በኩል ትልቅ ክፍተት ይፈጥራል። በዚህም የተነሳ ህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አካባቢንና በውስጡ የሚኖሩ ህይወት ያላቸው ነገሮች መስተጋብርም ጭምር ያዛባል። መደኃኒቶች በተገቢ ሁኔታ ካልተቀመጡና ለህክምና ካልዋሉ እንዲሁም በአግባቡ እንዲወገዱ ካልተደረጉ በአካባቢያችን (አፈር፣ውሃ እና አየር ውስጥ) የሚኖሩ ጠቃሚ የሆኑ ረቂቅ ተህዋስያንን ይጎዳሉ። በተጨማሪም በተፈጥሯቸው በሽታ አምጭ ያልሆኑ ተህዋስያን (oporchunistic pathogens) በሰውና በእንስሳት ላይ በሽታ እንዲያስከትሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በሌላ በኩል እነዚህ ተህዋስያን መድኃኒቱን ይላመዱና ለህክምና አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

**ፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች በአካባቢ ሥነ ምህዳር ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ የሚይሳይ ዲያግራም**




## 7.3. በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ችግር

እንስሳትና የእንስሳት ምርት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት የውጭ ምንዛሬ ከምታገኝባቸው ምርቶች ውስጥ የቁም እንስሳት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶችና ስጋ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን አገሪቱ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዳትሆን የሚያደርጉ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ የእንስሳት ጤንነትና ምርታማነትን በመቀነስ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል፡፡ በህገወጥ መንገድ ለተጠቃሚው የሚደርሱ የእንስሳት መድኃኒቶች በሽታን የመፈወስ አቅማቸው ዝቅተኛ ሊሆን ስለሚችል ላላስፈላጊ ወጪ ሊዳሪግ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በኮንትሮባንድ የሚገቡ መድኃኒቶች ከቀረጥ ውጪ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ህገ ወጥ ነጋዴዎች ግብር ስለማይከፍሉ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በዚህም የተነሳ በህገ ወጥ መንገድ ወደግብይት የሚገባ መድኃኒት በዋጋ ደረጃ ሊቀንስ ስለሚችል ተጠቃሚው ፊቱን ወደህገወጥ ንግዱ እንዲያዞር ያደርገዋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ነጋዴዎች በችርቻሮ ስም የብቃት ማረጋገጫና ንግድ ፈቃድ አውጥተው የጅምላ

አከፋፋይ ስራ በመስራት መንግስት ማግኘት የሚገባዉን የግብር ገቢ ከማሳጣቱም ባለፈ በዘርፉ በጅምላ አከፋፋይነት የተሰማሩ ድርጅቶችን ጥቅምና የሥራ ተነሳሽነት ይቀንሳል፡፡

## 8. ህገ- ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን ለመግታት መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች

ለህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር መስፋፋት መንስኤ ተብለው ለተቀመጡ ነጥቦች እንደአስፈላጊነቱ ለእያንዳንዳቸው ምላሽ መስጠት ከተቻለ መፍትሄ ማምጣት እንደሚቻል ታሳቢ ይደረጋል፡፡ ስለሆነም ዘርፉን በበላይነት የሚመራው የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ህገ ወጥ የመድኃኒት ንግድና ዝውውርን ለመቆጣጠር ከአጎራባች አገሮች ጋር ጥብቅ ትስስር መፍጠርና በአገር ውስጥም የእንስሳት ንግድና ዝውውሩ በሚፈለገው መንገድ እንዲሆን በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን በማጎልበት፣ በማስተባበር እና ግንዛቤ በመፍጠር አገራዊ ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ግድ ይለዋል፡፡ እናም በእያንዳንዱ መንስኤዎች መወሰድ የሚገባቸውን የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፡፡

### 8.1. የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳዳግ

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በእንስሳትና በማህበረሰብ ጤና ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት ባሻገር ለእንስሳት ምርትና ምርታማነት መቀነስ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለውና ከዚህ የተነሳ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያስከትል ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በህገ ወጥ ንግዱና ዝውውሩ መሳተፍ እንደሌለባቸው በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ በቂ ግንዛቤ መፍጠር የሚቻል ከሆነ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውሩን በዘላቂነት ማስወገድ እንደሚቻል መናገር ይቻላል፡፡ ስለሆነም በየደረጃው ለሚገኙት ባለድርሻ አካላትና አጠቃላይ ህብረተሰብ በተለያዩ የግንዛቤ መስጨበጫ መንገዶች( ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት፣ በተለያዩ ሚዲያዎች መልዕክቶችን በማስተላለፍ፣ በተለያዩ ብሮሸሮች፣ፖስተሮችና መፅሄቶች መልዕክቶች እንዲተላለፉ በማድረግ፣ ከተለያዩ መ/ቤቶች የተውጣጣ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ እንዲቋቋም በማድረግና ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ቁጥጥርን በመደበኛ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ ማካተት ) የማያቋርጥና ቀጣይነት ያለው ትምህርት በመስጠት ስለ ህገ ወጥ የእንስሳት ንግድና ዝውውር የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ይቻላል፡፡

## 8.2. የእንስሳት መድኃኒት አቅርቦትን ማሻሻል

የእንስሳት መድኃኒት በጥራትና በመጠን እንዲሻሻል ለማድረግ በመንግስት በኩል ለእንስሳት መድኃኒት የሚመደበውን በጀት ከፍ በማድረግ በቂና ጥራት ያለው መድኃኒት ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአገሪቱ ውስጥ የሚከሰቱ በሽታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ባለሀብቶች ጥራት ያለው መድኃኒቶችን ወደአገር እንዲያስገቡ የማበረታታት ስራዎች መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር በሁሉም ቦታዎች አርሶ/አርብቶ አደሩን ጨምሮ በየአካባቢው በቂና ጥራት ያለው መድኃኒት እንዲያገኝ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ተቋማት እንዲቋቋሙ ማድረግና ተደራሽነቱን ማስፋፋት፡፡

## 8.3. የእንስሳት ህክምናን ተደራሽነት ማስፋፋት

በአሁኑ ወቅት በእንስሳት ጤናው ዙሪያ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ለማቃለል በመንግስት በኩል ዘርፈ ብዙ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በአገሪቱ በሚገኙ በተለያዩ የትምህርት ተቋማት የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን በማሰልጠን የእንስሳት ሀብቱ በብዛት በሚገኝበት በአርሶ/አርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲመደቡ በማድረግ ችግሩን ለማቃለል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች ተደራሽነቱን ለማቃለል በአንዳንድ ክልሎች( አማራ ክልል) እየተሰራ ያለውን በእያንዳንዱ ቀበሌ የእንስሳት ጤና ባለሙያ በመመደብ አርሶ አደሩ በአካባቢው አገልግሎቱን እንዲያደኝ እየተደረገ ያለውን ተሞክሮ ወደ ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች በማስፋት ችግሩ እንዲቀንስ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለይም የእንስሳት ህክምና ተደራሽነትና የእንስሳት ጤና ባለሙያ እጥረት በሚታይበት አርብቶ አደር አካባቢዎች ለማህበረሰብ አቀፍ እንስሳት ጤና ሠራተኞች ተጨማሪ ስልጠናዎችን በመስጠት በስራው ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግና በአካባቢው በዘርፉ ባለሃብቶች እንዲሰማሩ በማድረግ ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ይቻላል፡፡

## 8.4. የሙያ ስነ-ምግባር ጉድለትን ማሻሻል

በሙያ ስነ-ምግባር በኩል የሚታየውን ክፍተት ለማሻሻል ለባለሙያዎች በእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም በህገ ወጥ መድኃኒት ንግድና ዝውውር ትምህርት በመስጠት ግንዛቤ እንዲያዝበት ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጪ የሙያ ስነ-ምግባሩን በማያከብሩ

ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ስነ-ምግባር እንዲሻሻል ማድረግ ይቻላል።

## 8.5. የንግድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

በእንስሳት መድኃኒት ንግድና ግብይት በኩል በአገሪቱ ውስጥ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በሁሉም አካባቢዎች ሊተገበር የሚችልና አሰራሮችን የሚያቀላጥፍ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እንዲሁም የአስተዳደርና የቁጥጥር ስራዎችን በተሳለጠ መልኩ በመተግበር የንግድ ሁኔታዎች ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል። ሆኖም ግን ብዙ ህጋዊ የእንስሳት መድኃኒት ነጋዴዎች በተደጋጋሚ እንደሚያነሱት የአገሪቱ የጉምሩክ አሰራር የተቀላጠፈና ከኪራይሰብሳቢነት መንፈስ የፀዳ ስላልሆነ በንግድ ዘርፉ ለመስራት ተነሳሽነትን አይፈጥርም። ስለሆነም ሁሉም በየደረጃው የሚገኘው ባለድርሻ አካል በመተባበርና አብሮ በመስራት የቁጥጥር ጣቢያዎችን በሰው ሀይልና ዘመናዊ በሆነ አሰራር ማደራጀትና ሠራተኞችን በመልካም ስነ ምግባር በማነጽ ለችግሩ መፍትሔ ማበጀት ያስፈልጋል።

## 8.6. ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን በዘላቂነት ለመቆጣጠር የሁሉንም ህብረተሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በህገወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ቁጥጥር ከአጎራባች አገሮች፣ ከባለድርሻ አካላት፣ በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ከተሰማሩ ባለሀብቶች፣ ከእንስሳት ጤና ባለሙያዎች እና ከህብረተሰቡ ጋር ትስስርና ቁርኝት በመፍጠር ያላሰለሰና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዲሰጥ በማድረግ ሁሉም በየደረጃው ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግ ይቻላል። በዚህ ረገድ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከርና እንዲጎለብት በማድረግ ህገወጥ ንግድና ዝውውሩን በዘላቂነት መቆጣጠር የሚያዳግት አይሆንም።

## 8.7. የቁጥጥር ተግባራትን ማጠናከር

በእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም በህገ ወጥ መድኃኒት ንግድና ዝውውር ዙሪያ በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር ከተቻለ ህገወጦች ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ ማድረግ ይቻላል። የባለስልጣኑና የክልል ተቆጣጣሪ አካላት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በህገ ወጦች ላይ ያላሰለሰ ክትትልና ትምህርት መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ ውጪ በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውሩ ቁጥጥር የሁሉንም ማህበረሰብ ያላሳለሰ ትግልና

ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ፖሊስ፣ ፍትህ፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የመድኃኒት ምግብና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ ጤና ሚኒስቴር፣ የእንስሳት ጤና እና መድኃኒት ንግድ ባለሙያዎች) የተውጣጣ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ በየደረጃው በማቋቋም የቁጥጥር ተግባሩን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ችግሩ ጎልቶ በሚታይባቸው ቦታዎችና አካባቢዎች (ምስራቃዊ የአገሪቱ ክፍሎች ሶማሌ፣ ሀረርና ድሬዳዋ ባሌ፤ ቦረና፤ ሞያሌ ፣ መተማ) ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቋቋም በማድረግ ከአጎረባች አገሮች የቁጥጥር አካላት ጋር መረጃ በመለዋወጥና በጋራ በመስራት ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ላይ የተሰማሩ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች ስላመረቷቸው፣ስላስመጧቸው፣ ስለላኳቸው፣ ስላከፋፈሏቸውና በችርቻሮ ለተጠቃሚው ስላደሏቸው መድኃኒቶች ሪከርድ በመያዝ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ ለቁጥጥር ሥራው መሳካት የድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

## 8.8. ህጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን በዘላቂነት ለማስወገድ ዋናው ሥራ የሚሆነው በህገ ወጥ ተግባሩ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን እና የአጠቃላይ ማህበረሰቡን ግንዛቤ መለወጥ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ህገ ወጦች ከተግባራቸው የማይመለሱ ከሆነ የእንስሳት መድኃኒትን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ባለማክበር በህገ ወጥ መንገድ ያላግባብ ለመተግበር በሚሞክርና በተገበረ ማንኛውም ግለሰብ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ በአዋጅ 728/2004 አንቀጽ 26 ስር የተቀመጡ ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ሀ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 21 የተሰየመን ተቆጣጣሪ ሥራ የሚያውክ ከሆነ ከ6 ወር በማያንስ ቀላል እስራት እና ከብር 10 ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እንደሚያሰቀጣና በዚሁ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተቀመጠው መሠረት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የሙያ ፈቃድ አግባብ ያለውን አካል ሳያስፈቅድ ለሌላ ሰው አሳልፎ ከሰጠ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከብር 5ሺ በማያንስና ከብር 20ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ለ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት አምራች፣ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ፈቃድ ለሌለው ሰው መድኃኒት ካከፋፈለ ከሁለት ዓመት

በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 10.000.00 በማያንስና ከብር 20.000.00 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሐ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ማንኛውም ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይኖረው በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ሥራ ከተሰማራ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 20ሺ. በማያንስና ከብር 50ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

መ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ማንኛውም በእንስሳት መድኃኒት ጅምላ ወይም ችርቻሮ ንግድ የተሰማራ ሰው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠው ሰው መድኃኒት ከገዛ ከሁለት ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 10ሺ. በማያንስና ከብር 20ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሠ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የእንስሳት መድኃኒት አስመስሎ ያቀረበ ወይም የከለሰ ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበትን መድኃኒት ለገበያ ያቀረበ ሰው ከ10 ዓመት በማያንስና ከ 20 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 20ሺ. በማያንስና ከብር 50ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ረ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ማንኛውም የሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት እና ከብር 10ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

ሰ. በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት ማንኛውም ከእንስሳት መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ጋር የተገናኙ ሥራዎችን የሚያከናውን አግባብ ያለው አካል ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን ወይም ተገልጋይ መደለያ በመቀበል/በመስጠት ወይም በዝምድና ወይም በሌላ ግንኙነት ሳቢያ በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ከተደነገገው ውጭ፡-

ሀ/ የእንስሳት መድኃኒት ንግድን በተመለከተ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወይም የሙያ የሥራ ፈቃድ የሰጠ/የወሰደ ወይም ያደሰ ወይም እንዲሰጥ ወይም እንዲታደስ ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የእንስሳት መድኃኒትን የጥራት፣ የደህንነት እና እንደአግባቡ የፈዋሽነት ደረጃ ግምገማ ሳያልፍ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደረገ ወይም እንዲፈቀድ ያደረገ እንደሆነ፤

ከ 10 ዓመት በማያንስና ከ 15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እና ከብር 30ሺ. በማያንስና ከብር 50ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ በማስቀመጥ ይህንን ጥፋት በመፈጸም

ተግባር የተሳተፈ ሰው ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው ጥፋትና ስለተባባሪዎቹ ሚና በቂ መረጃ ከሰጠ የፍትህ ሚኒስቴር ወይም የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ እንዳይመሰረትበት ሊያደርግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

## 9. በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ቁጥጥር የባለድርሻ አካላትና የተገልጋዩ ተግባርና ኃላፊነት

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ተግባራትን በዘላቂነት ለመቆጣጠር በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዩ ህብረተሰብም ጭምር የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

### 9.1. ባለስልጣን መ/ቤቱ

- ✓ ስለመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም ስለ ህገ ወጥ መድኃኒት ንግድና ዝውውር ብሎም ስለሚያስከትለው ጉዳት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲፈጠርበት ለባለድርሻ አካላትና ለተገልጋዩ/ህብረተሰቡ/ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፡፡
- ✓ ስለ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ከአጎራባች አገሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ክልል ተሻጋሪ በሆኑ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
- ✓ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ በየደረጃው እንዲቋቋም ያስተባብራል ተግባሩንም ይከታተላል፡፡
- ✓ ቅርንጫፍ መ/ቤት የሚያስፈልግባቸው ቦታዎችን በጥናት በማረጋገጥ ቅርንጫፍ መ/ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡
- ✓ በህገ ወጥ ንግድና ዝውውር ላይ በተሳተፉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል እንዲወሰድም ያስደርጋል፡፡
- ✓ በህገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር የተገኘን የእንስሳት መድኃኒት እንዲወረስ ያደርጋል/ያስደርጋል፡፡
- ✓ የቁጥጥር መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ በተዋረድም ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፡፡

## 9.2. የክልል እንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ/ግብርና ቢሮ/

- ✓ በክልል ውስጥ ስለሚካሄድ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ግብይት የአስተዳደራዊና ቁጥጥር ሥራዎችን ይሰራሉ፡፡
- ✓ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ግብይት በአገሪቱ ውስጥ መስመር እንዲይዝና የተሳለጠ እንዲሆን ከእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመተባበር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ የቁጥጥር ስራው ዘላቂነት እንዲኖረው እንደ ማንኛውም መደበኛ ሥራ ቼክሊስት በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ✓ ስለእንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም ስለ ህገ ወጥ ንግድና ዝውውር ለባለድርሻ አካላት፣ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሃብቶች፣ ለባለሙያዎችና ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡
- ✓ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ እንዲቋቋም ያደርጋል፤ እያንዳንዱ ኮሚቴም በቁጥጥር ተግባሩ ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ያስተባብራሉ፡፡
- ✓ ከአጎራባች አገሮች ጋር በህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር ቁጥጥር ዙሪያ በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ✓ የመድኃኒት አቅርቦት እጥረትን ለማቃለል ህጋዊ የመድኃኒት ንግድ ድርጅቶች በየአካባቢው እንዲቋቋሙ በማበረታታት ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ የእንስሳት መድኃኒትን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል በሚዘጋጁ መመሪያዎች መሠረት የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ግብይትን ማስተዳደርና መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ በህገ ወጥ ንግድና ዝውውር ላይ ተሳትፈው በተገኙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ትምህርት ከመስጠት ባለፈ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፡፡
- ✓ በህገ ወጥ ንግድና ዝውውር በኩል ስለሚሰሩ የቁጥጥር ስራዎች በየጊዜው ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 9.3. የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን ለመቆጣጠር ሁሉም በየደረጃው የሚገኘው ህብረተሰብ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ እስከ ታች

በየደረጃው የሚገኙ የሙያው ባለቤት የሆኑት የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በዘርፉ የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሆነም፡-

- ✓ ስለ እንስሳት መድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም ስለህገወጥ መድኃኒት ንግድና ዝውውር አስከፊነትና የሚያስከትለውን ጉዳት በየደረጃው ለሚገኘው አጠቃላይ ህብረተሰብ ያላሰለሰ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣሉ፡፡
- ✓ በየደረጃው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ የቁጥጥር ኮሚቴ እንዲቋቋም ያስተባብራሉ፤ ከኮሚቴው ጋርም የቁጥጥር ስራውን በቅንጅትና በዘላቂነት ይሰራሉ፡፡
- ✓ ስለመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀም የወጡ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን መሠረት በማድረግ ስራዎቻቸውን መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ✓ በቁጥጥር ተግባሩ በኩል የሚሰሩ ሥራዎችን ሁልጊዜ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ ከቁጥጥር ኮሚቴው ጋር በመሆን ህገወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በሚያካሄዱ ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ቁጥጥር ያደርጋሉ፤ የእርምት እርምጃም እንዲወሰድ ያደርጋሉ፡፡

## 9.4. ባለድርሻ አካላት

ምንም እንኳን ዘርፉን በበላይነት የሚያስተዳድርና የሚቆጣጠር ባለስልጣን መ/ቤት የተቋቋመ ቢሆንም ብቻውን ያለባለድርሻ አካላት ቅንጅት ፋይዳ ያለው ሥራ መስራት እንደማይችል ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት፡-

- ✓ ከባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲሁም ከክልል እንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ኤጀንሲ/ግብርና ቢሮ/ ጋር በቅንጅት ለመስራት መተባበር ይኖርበታል፡፡
- ✓ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና የቁጥጥር ግብረ ሀይል ኮሚቴ ውስጥ በመሳተፍ ስራውን በዘላቂነት ለመስራት በቁርተኝነት መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡

- ✓ ስራው ከመደበኛ ስራ ጎን ለጎን እንዲሰራ የድርጊት መርሃ ግብር/ቼክሊስት/ በማዘጋጀት ችግሩን በዘላቂነት ለማስወገድ መረባረብ፡፡
- ✓ የችግሩን አስከፊነትና የሚያስከትለውን ጉዳት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ በህገወጥ ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ የእርምት እርምጃ ይወስዳል እንዲወሰድም ያደርጋል፡፡
- ✓ ስለሥራው አጠቃላይ መረጃዎችን በመያዝ ለሚመለከተው አካልና ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡
- ✓ በቁጥጥር ስራዎች ላይ ግንዛቤዎችን ለመጨበጥ ከባለስልጣን መ/ቤቱ የአሰራር መመሪያዎችና በተጓዳኝ ስልጠናዎች እንዲሰጡት ይጠይቃል፡፡

## 9.5. በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች/ባለሃብቶች

በህጋዊ መንገድ ተቋቁመው በእንስሳት መድኃኒት ንግድ ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች እራሳቸውን ብሎም አገራቸውን ለመጥቀም፡-

- ✓ በህጋዊ መንገድ ከባለስልጣን መ/ቤቱ የተገኘ የሙያ ፍቃድና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያዘጋጀውን የአሰራር መመሪያ አክብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ✓ ህገወጦች ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ በማድረግ በአገሪቱ መልካም የግብይት ስርዓት እንዲስፋፋ የበኩላቸውን ማበርከት አለባቸው፡፡
- ✓ ህገወጦችን በማጋለጥ ለሚመለከታቸው የቁጥጥር አካላት እንዲሁም ለባለስልጣን መ/ቤቱ መጠቆም ይኖርባቸዋል፡፡

## 9.6. ተጠቃሚው ህብረተሰብ

የህገወጥ ንግዱና ዝውውሩ የመጨረሻው መዳረሻ ህብረተሰቡ ነው፡፡ ይህም የሚያሳው ለህገወጥ ንግድና ዝውውር ህብረተሰቡ እንደመሸሸጊያ እንደሚያገለግል ነው፡፡ ስለዚህ ህብረተሰቡ፡-

- ✓ መድኃኒቶችን መጠቀም ያለበት አካባቢው ከሚገኘው የእንስሳት ጤና ክሊኒክ ወይም የእንስሳት መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች መሆን ይኖርበታል፡፡
- ✓ መድኃኒቶችንም ሲገዙና ሲጠቀሙም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎችን በማማከር መሆን ይኖርበታል፡፡

- ✓ ከማንኛውም ቦታና ገበያ ላይ እንዲሁም ባለሙያ ካልሆነ ግለሰብ መድኃኒቶችን ገዝተው መጠቀም የለባቸውም፡፡
- ✓ በእንስሳት ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ ብቻ የሚሰጡ መድኃኒቶችን በራሳቸው ገዝተው መጠቀም የለባቸውም፡፡
- ✓ በህገወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር የሚሳተፉ ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን ለሚመለከተው አካል በመጠቆም ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ በማድረግ የህገወጥ ንግዱና ዝውውሩ እንዲቀንስ የበኩላቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

## 10. ማጠቃለያ

ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር በሀገራችን በሁሉም አካባቢዎች የሚታይ ቢሆንም በጎረቤት አገሮች አዋሳኝ የሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በስፋት ይስተዋላል፡፡ የግንዛቤ እጥረት፣ የመድኃኒት አቅረቦት ማነስና የቁጥጥር ስርዓቱ ጠንካራና የተደራጀ አለመሆን ለችግሩ መስፋፋት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ነጋዴዎች የቁጥጥር ቦታዎችን ለማለፍ የፍተሻ ሰራተኞችን በጥቅም መደለልን ጨምሮ የተለያዩ የማጭበረበሪያ መንገድ ይጠቀማሉ፡፡ የማህበርሰብ እንስሳት ጤና ባለሙያዎች፣የሰው መድኃኒት ንግድ ድርጅቶች፣ ሌሎች የሸቀጣሸቀጥ ነጋዴዎች የህገ ወጥ ንግዱ ዋና አካላት ናቸው፡፡ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድ የእንስሳትን ጤና ችግር በማባባስ ሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ከቁም እንስሳት ሽያጭ እና ከእንስሳት ተዋጽኦ የምታገኘውን ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፡፡ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውር አግባባዊ የመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀምንም በማዳከም የበሽታ አምጪ ተህዋስያን መድኃኒትን እንዲላመዱ ያደርጋል፡፡ ይህ ችግር የህበረተሰቡን ጤና በመጉዳት ብሎም የእንስሳት መድኃኒት ተጠቃሚዎችን ላላግባብ ወጭ በመዳረግና ሀገሪቱ ከቀረጥና ግብር ማግኘት የሚገባትን ገቢ በመቀነስ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ እያስከተለ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መንግስት፣ ባለድርሻ አካላትና ሁሉም ህብረተሰብ ከባለስልጣኑ ጋር በቅንጅት በመስራት፣ የመድኃኒት አቅርቦትን በማሻሻል፣ ለእንስሳት መድኃኒት ነጋዴዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠርና ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ህገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ንግድና ዝውውርን የመከላከል ሀገራዊ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡